# የመንግስት የልማት ድርጅቶች የኮርፖሬት ማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 505/2013

Guidelines for Corporate Social Responsibility Service Delivery by Government Development Organizations (Directive No. 505/2013)

የመንግስት ልማት ድርጅቶች ይዞታ እና አስተዳደር
Public Enterprises Holding and Administration

ጥር 1፥ 2011

## መግቢያ

የመንግስት ልማት ድርጅቶች የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማሳካት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ባላቸው ሚና ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊ እንዲሁም የሰራተኛውንና የማህበረሰቡን ጤንነትና ደህንነት የመጠበቅ ሃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ፤

የመንግስት ልማት ድርጅቶች ዓላማቸውን ለማሳካት ከሚያደርጉት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጐን ለጐን የማህበረሰቡ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሥራቸው አንድ አካል አድርገው ሲወስዱና ከማህበረሰቡ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ሲፈጥሩ ለህልውናቸው ዋስትና አንዱ ማረጋገጫ በመሆኑ፤

በአሁኑ ወቅት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የተለያዩ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ቢሆንም የማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ የሚመራበት ወጥነት ያለው አሰራር መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

በሌላ በኩል በአለም አቀፍ ደረጃ ሊባል በሚችል ሁኔታ ተገቢውን ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት የሚሰጡ የልማት ድርጅቶች የፍትሃዊነት አሰራርስርዓት መተግበራቸውአንዱ ማሳያ ተደርጎ ስለሚወሰድ፤

በዚህም መሰረት የማህበራዊ ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት አለምአቀፍ ግዴታ እየሆነ የመጣና ይህንን ሥርዓት ተግባራዊ የሚያደርጉ የልማት ድርጅቶች በማህበረሰቡ ያላቸውንተቀባይነት የሚያጠናክር በመሆኑ፤

ዓለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ በልማት ድርጅቶች ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ የልማት ድርጅቶችን ተጠቃሚነት የሚያጠናክር በመሆኑ፤

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኤጀንሲውን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው ደንብ ቁጥር 445/2011 አንቀጽ (5) ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚመራበትን ይህንን የኮርፖሬት የማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## I. አጭርርዕስ

ይህ መመሪያ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር **505/2013** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## II. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ኤጀንሲ" ማለት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታ እና አስተዳደር ኤጀንሲነው፡፡
2. **"የመንግስት ልማት ድርጅት"** ማለት በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/84 አንቀጽ 2(1) የተመለከተውን ትርጓሜ የሚያሟላ ድርጅት ወይም አክሲዮኖቹ ሙሉ በሙሉ በመንግስት ባለቤትነት የተያዙ አክሲዮን ማህበር ሲሆን በሌሎች ህጎች ወይም በመንግስት ውሳኔ የተለየ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የተሰየመላቸውን ድርጅቶች አይጨምርም፡፡
3. **"ቦርድ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 25/84 አንቀጽ 10(2) እና አንቀጽ 12 መሰረት የመንግስት የልማት ድርጅቶችን በበላይነት እንዲመራ፣ እንዲቆጣጠርና ውሳኔ እንዲሠጥ የሚመደብ የልማት ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ ነው፡፡
4. **"የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት"** ማለት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላሉበት የአካባቢ ህብረተሰብ ያለባቸውን ችግሮች ባላቸው አቅም በማቃለል ወይም በህግና ደንብ የተቀመጡ ማኅበረሰብ ነክ ግዴታዎችን ለመወጣት ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ውጤት ያላቸውን ተግባራት በመፈፀም የሚሰጡት አገልግሎት ነው፡፡
5. **"ማኔጅመንት"** ማለት ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና ተጠሪነታቸው ለዋና ሥራ አስፈፃሚ የሆኑ የድርጅቱ የሥራ አመራር አባላት ናቸው፡፡

## III. የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን፡-

ይህ መመሪያ ሙሉ በሙሉ በመንግስት ሆነው በኤጀንሲው የሚተዳደሩ የልማት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## 2. መመሪያው የሚመለከታቸው አካላት ሃላፊነት፤

### 2.1 የኤጀንሲው ተግባርና ኃላፊነት፤

2.1.1 የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥመመሪያ ያወጣል፣ በሁሉም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተግባራዊ እንዲደረግ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

2.1.2 በድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ የሚቀርበውን የድርጅቱን ስትራቴጂክና ዓመታዊ የኮርፖሬትማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎትአሰጣጥ ዕቅድ ያጸድቃል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

2.1.3 የማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አፈጻጸም የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ በሚታዩ ክፍተቶች የማስተካከያ ዕርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

2.1.4 ከልማት ድርጅቶች ወቅታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶች እንዲቀርቡ ያደርጋል፣ አፈጻጸማቸውን በመምገም ተገቢውን ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል፤

### 2.2 የሥራ አመራር ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት፤

2.2.1 የልማት ድርጅቱ የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከተታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

2.2.2 የኮርፖሬት ማህበራዊኃላፊነት አገልግሎት ተግባራዊ የሚሆንበት አቅጣጫ፣ አግባብ፣ ወሰን እንዲሁም ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮችን ይወስናል፤

2.2.3 የድርጅቱየኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት ስራዎች በስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ መካተታቸውን ያረጋግጣል፣አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማል አቅጣጫ ይሰጣል፤

2.2.4 የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት ሥራዎችን ለመፈፀም የሚያስፈልግ በጀት ለኤጀንሲው በማቅረብ ያፀድቃል፤

2.2.5 የማህበራዊ አገልግሎት ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ ተግባራትን አፈጻጸም በየወሩ እና በየሩብ ዓመት በመገምገም ውጤቱ በወቅታዊ ሪፖርት ተካቶ ለኤጀንሲው እንዲቀርብ ያደርጋል፤

2.2.6 ኤጀንሲው ያወጣውን የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ በተሟላ ሁኔታ ሥራ ላይ ስለመዋሉ ይቆጣጠራል፣ በአግባቡ ስራ ላይ ባይውል ቦርዱ ተጠያቂ ይሆናል።

## 2.3 የልማት ድርጅቱ የሥራ አመራር (ማኔጅመንት) ተግባርና ኃላፊነት፤

2.3.1 የልማት ድርጅቱ የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ አፈጻጸሙን ለቦርድ ሪፖርት ያደርጋል፤

2.3.2 የድርጅቱን የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት ሥራዎች በስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ እንዲካተትና ተገቢው የሠው፣ የማቴሪያልና የፋይናንስ ሃብት ለቦርድ አቅርቦ ያፀድቃል፤

2.3.3 እንደ ልማት ድርጅቱ ስፋትና ባህሪ የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ በበላይነት የሚያስተባብር የስራ ክፍል እንደ አስፈላጊነቱ ያቋቁማል፤

2.3.4 የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት ስራዎች በስትራቴጂክዕቅድ እናበድርጊት መርሀ-ግብሮች መሰረት ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑን በመከታተል ለቦርድሪፖርት ያቀርባል፤

2.3.5 ለአመራሩና ለሰራተኛው በኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፤

2.3.6 የማህበረሰቡንና የባለድርሻ አካላትን ኃላፊነትና የሚኖራቸውን ሚና በተመለከተ የጋራ ዓላማ እንዲያዝና መግባባት እንዲፈጠር ያደርጋል፣ በዕቅድ ዝግጅትና ግምገማም ያሳትፋል፤

2.3.7 የድርጅቱን ሰራተኞች ደህንነት በማስጠበቅና የአካባቢ ማህበረሰብን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት እንዳግባቡ በመቅረጽ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣ ሪፖርትም ያቀርባል።

## 2.4 የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያስተባብር የስራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት፤

2.4.1 መመሪያው ተግባራዊ እንዲሆን ፈፃሚ አካላትን ያስተባብራል፣ የሚወጡ ፕሮግራሞችን ከሥራ አመራሩ በሚሰጠው አቅጣጫ በበላይነት ይመራል፤

2.4.2 ከሚመለከታቸው አካላት የሚቀርቡ የድጋፍ ጥያቄዎች በመመሪያው መሰረት ምላሽ እንዲያገኙ ይከታተላል፤

2.4.3 የድርጅቱን ዓመታዊ የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥዕቅድና ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፣ለበላይ አመራር አቅርቦ ያስፀድቃል፤

2.4.4 የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት ጥያቄዎችን በመመሪያው በተቀመጠው መስፈርት መሠረት ይገመግማል፣ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል።

2.4.5 የሥራ ክፍሉ ተቀባይነት ላላቸውም ሆነ ተቀባይነት ለሌላቸው የማህበራዊ አገልግሎት የድጋፍ ጥያቄዎች የግምገማ ሪፖርት ለዋና ስራ አስፈጻሚ ያቀርባል።

## ክፍል ሦስት

## 3. የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አተገባበር ሂደት፤

### 3.1 የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነትአገልግሎት የትኩረት መስኮች፤

በአገሪቱ ህጎችና ደንቦች የተደነገጉ ግዴታዎችና ሃላፊነቶች እንደ ተጠበቁ ሆነው የልማት ድርጅቱ ከዚህ በታች በተገለጹ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥተው መስራት የሚጠበቅባቸው ይሆናል፡-

3.1.1 የማህበራዊ ድጋፎች / Social Support/

3.1.2 የኢኮኖሚያዊ ድጋፎች / Economic Support/

3.1.3 የአካባቢ ድጋፍ / Environmental Support/

### 3.2 የኮርፖሬት ማህበራዊ አገልግሎት መርሆዎች፤

3.2.1 አንድ ድርጅት የተቋቋመለትን አላማ ለማሳካት በሚንቀሳቀስበት ጊዜ በሠራተኛ ደህንነት፣ በአካባቢ እና በህብረተሰብ ላይ ጉዳት ወይም አሉታዊ አመለካከት የሚፈጥር ተግባር መፈፀም የለበትም፤

3.2.2 አንድ ድርጅት አካባቢን በመጠበቅና የህብረተሰቡን እምነት በማትረፍ ዘላቂ ህልውናውን ማስቀጠል መቻል አለበት፤

3.2.3 አካባቢን በመጠበቅ /በመንከባከብ፣ የሠራተኛ ደህንነት በማስጠበቅ ሂደት ያከናወናቸውን ተግባራት ወይም ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተጋገዝ ያስገኘውን ውጤት በማሳወቅ መልካም ገጽታውን መገንባት አለበት፤

3.2.4 በማህበራዊ አገልግሎት ስም የሀብት ብክነት እንዳይከሰት ጥንቃቄ መደረግ አለበት፤

### 3.3 ዘላቂ የልማት ግቦችና የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት ትግበራ ፤

የልማት ድርጅቶች የሚያከናውኗቸው የማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት ተግባራት የዘላቂ ልማት ግቦች/Sustainable Development goals/ ላይ የተመሰረቱ ሆነው የልማት ድርጅቶችን አቅም ያገናዘቡ ሊሆኑ ይችላሉ።

## 3.4 የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት የፋይናስ ምንጭ፤

3.4.1 የልማት ድርጅቱ ያለፈው በጀት ዓመት ትርፋማ አፈጻጸም ሲኖረው በዓመታዊ ዕቅድ ላይ ለኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት የሚውል በጀት መያዝ አለበት።

3.4.2 ትርፋማ አፈጻጸም የሌለው ነገርግን በባህርይው የማህበረሰብ ድጋፍ እንዲያደርግ የሚገደድከሆነ ካለው አቅም ጋር በማጣጣም የኮርፖሬት ማህበራዊ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችለውን በጀት መያዝ ይጠበቅበታል፤

3.4.3 በአፈጻጸሙ ትርፋማ ያልሆነ የልማት ድርጅት ለኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት ማከናወኛ በጀት የማይጠይቁ እና በድርጅቱ አቅም ሊፈጸሙ በሚችሉ ድጋፎች ላይ መሳተፍ ይኖርበታል፤

3.4.4 ከተለያዩ ተቋማት በሚገኝ የብድር ገንዘብ መነሻ በአበዳሪዎች አስገዳጅ ውሉታ የተገባባቸው የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት ተግባራትን የልማት ድርጅቱ ሊፈጽም ይገባል፤

## 3.5 የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎትዕቅድ፤

የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት ዕቅድን ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ዕቅዱ በሚከተለው መሠረት መዘጋጀት ይኖርበታል።

3.5.1 በጥናት የተለዩ እና ቅድሚያ ትኩረት የተሠጣቸው የኮርፖሬት ማህበራዊ አገልግሎት ጉዳዮች ዝርዝር መለየት፤

3.5.2 በጥናት የተለዩ እና ቅድሚያ ትኩረት የተሠጣቸው የኮርፖሬት ማህበራዊ አገልግሎት ጉዳዮችከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመወያየትሊለኩ የሚችሉ ዓላማዎችን በማስቀመጥ በዕቅድ ማካተት፤

3.5.3 የተቋሙንና የባለድርሻ አካላትን ሚና በግልጽ ለይቶ የሥራና የሃላፊነት ድርሻበግልጽ ማስቀመጥ፤

3.5.4 በዕቅድ የተያዙ ድጋፎችን ለመተግበር የሚያስፈልጉ ወጪዎችን መወሰንና በጀት አስፀድቆመመደብ፤

3.5.5 የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥዕቅድና መርሀ ግብር ማዘጋጀት፤

3.5.6 የዕቅዱን የድጋፍና ክትትል ስርዓት መዘርጋት።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Public Enterprises Holding and Administration Agency

## ክፍል አራት

### 4. በኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ የተከለከሉ ተግባራት፤

4.1 ለኃይማኖት ተቋማት የሚደረግ ድጋፍ፤

4.2 የዘር፣የቀለም ወ.ዘ.ተ ልዩነት ሊያስፉ ለሚችሉ ተግባራት የሚሰጥ ድጋፍ፤

4.3 ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚደረግ ድጋፍ፤

4.4 የህዝብ ደህንነትና ጸጥታ አደጋ ውስጥ ለሚከቱ እንቅስቃሴዎች የሚሰጥ ድጋፍ፤

4.5 የህዝብን ሞራል እና ዕምነት ለሚጻረር ድርጊት የሚሰጥ ድጋፍ፤

4.6 ድርጅቱን ለታወቀ ወይም ላልታወቀ ዕዳ የሚዳርግ ድጋፍ፤

### 5. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎችና አሰራሮች፤

መስከረም 2011 የወጣ የልማት ድርጅቶች የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ እንዲሁም ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛቸውም መመሪያና የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

### 6. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በኤጀንሲው ሊሻሻል ይችላል፡፡

### 7. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጥር 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**በየነ ገ/መስቀል**

**የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ**